የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት
ETHIOPIAN ENVIRONMENT AND FOREST RESEARCH INSTITUTE






# የዋና ዋና ዛፍ ዝርያዎች ምቹ ሥነ-ምህዳር፣ የዘር ባህሪያትና ጥቅሞች


የዛፍ ዘር ቴክኖሎጂ ማስተባበሪያ

ሰኔ 2012 ፤

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ









**ምስል፡-**

(ሀ) ጥሩ የጣውላ ዛፍ ዝርያ (ቀጥ ያለና ረጅም ንጹህ ግንድ ያለው እና ሌሎች ተያያዥ የጣውላ ባህርያት ያሉት)፣

(ለ) ጥሩ የውበት ዛፍ ዝርያ (ለዓይን የሚስብ እና ሌሎች ተያያዥ የተጠቃሚን ፍላጎት የሚያካትቱ)፣

(ሐ) ጥሩ የመኖ ዛፍ ዝርያ (ብዙ ቅጠል የሚይዝ፣ ከተቆረጠ በኋላ በቀላሉ የሚያቆጠቁጥ እና ሌሎች ተያያዥ የመኖ ባህርያት ያሉት)፣

(መ) ጥሩ የማገዶ ዛፍ ዝርያ (ብዙ እንጨት የሚሰጥና ሌሎች ተያያዥ የማገዶ ባህርያት ያሉት)፡፡

ይህ የዝርያዎች መግለጫ በኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት የዛፍ ዘር ቴክኖሎጂ ማስተባበሪያ ዘራቸው እየተሰበሰበ ለተጠቃሚ በመሰራጨት ላይ ያሉ ዋና ዋና የዛፍ ዝርያዎች ባህሪ መግለጫ ሲሆን በዋናነት ግን የዝርያዎቹ የዘር ባህሪ ላይ ያተኩራል፡፡

ይህን መግለጫ ተጠቃሚዎች በቀላሉ መረዳት የሚያስችላቸው ይሆን ዘንድ በአቀራቡም ይሁን በይዘቱ በዝርያዎቹ ላይ የተሻለ ልምድ ያላቸው ተጠቃሚዎችና ተመራማሪዎች አስተያታቸውን እንዲለግሱ ማስተባበሪያው ይጠይቃል፡፡ አስተያየቶችን፣ ማስተካከያዎችን እንዲሁም ማሻሻያዎችን ያካተተ ዕትም በየጊዜው ሊወጣ የሚችል መሆኑን እየገለጽን ለአስተያየታችሁ ከታች የተጠቀሰውን ኢሜል እንድትጠቀሙ ከምስጋና ጋር እንጠይቃለን፡፡

*አድራሻ፦*
*የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት*
*የዛፍ ዘር ቴክኖሎጅ ማስተባበሪያ*
*(ዶ/ር ይጋርዱ ሙላቱ)*

ፖ.ሣ.ቁ:- 30708, አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ስልክ: ቢሮ +251-116-456582, +251-116-476499, +251-116- 46 04 44, +251-116 -45 65 77, +251- 116-46 46 06፣ ሞባይል 251-911173640፤ ፋክስ: +251-116 -46 03 45, +251-116-442368፤ ዌብሳይት: http: //www.eefri.org፤ http://www.eefri.org/researches/tree-seed-technology-coordination/; tstc.eefri@gmail.com

## መግቢያ

ሃገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮና ብዝሃ ህይወት ሀብት እጅግ ከበለጸጉ ሃገራት አንዷና ዋነኛዋ ስትሆን ከነዚህ ጸጋዎችም የደን ሀብቷ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ አብዛኛው የሃገራችን ህብረተሰብም ኑሮው ከግብርና ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የደን ሃብት ጥገኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በደን ሃብት አጠቃቀምና ልማት ላይ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ከደን ሃብት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ የዛፍ ዝርያዎች እንደ ባህሪያቸው ዘርፈ ብዙ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ ያበረክታሉ፡፡

በመሆኑም ከደን የሚገኘውን ሃብት ሳይንሳዊ በሆነና ከፍተኛውን ጠቀሜታ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚቻለው የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች ያላቸውን ሥነ-አካላዊ እና አካባቢያዊ ባህሪ በመረዳትና ሥራ ላይ በማዋል ነው፡፡

ይህ የዛፍ ዝርያዎች ባህሪ መግለጫ የተመረጡና በስፋት እየተሰራጩ እንዲሁም በጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ የዛፍ ዝርያዎችን የዘር ባህሪ፣ ተስማሚ የሥነ-ምህዳር ቀጠና፣ የቅድመ-አዘራርና የአዘራር ዘዴ፣ እንዲሁም ጥቅም መግለጫ ያካተተ ሲሆን ለተለያዩ የዛፍ ዘር ተጠቃሚዎች መልካም የክህሎት እገዛ የሚያደርግ ጽሁፍ ነው፡፡

በተጨማሪም በሀገራችን በሚካሄዱ ዓመታዊ የዛፍ ተከላ ጊዜያት ችግኝ በመግዛት ወይም ከአቅራቢዎች በማግኘት ችግን መትከል የሚፈልጉ የህብረተሰብ አካላት ይህን መግለጫ በመጠቀም የትኛውን ዝርያ ለምን ጥቅምና የት አካባቢ ቢተክሉት የተሻለ እንደሚሆን ውሳኔ ለመስጠት ያግዛል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የዋና ዋና ዛፍ ዝርያዎች ምቹ ሥነ-ምህዳር፣ የዘር ባህሪያትና ጥቅሞች

| ሳይንሳዊ መጠሪያ | አካባቢያዊ መጠሪያ | ተስማሚ ስነምህዳር | አማካይ የዘር ቁጥር በኪ.ግ. | የዘር ባህሪ | የዘር ቅድመ መዝራት ህክምና | የአዘራር ዘዴ | የዝርያው ዋና ዋና ጥቅሞች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *Acacia abyssinica* | የአበሻ ግራር | 1500-2800 ሜ.ባ.ጠ.በ ወይና ደጋና ሁሉም ደጋ አካባቢዎች | 17763 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለከሰል፣ ለንብ ማነብ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለጥምር ደን እርሻ |
| *Acacia albida (Faidherbia albida)* | አልቢዳ ግራር፣ ገርቢ | ከ1500-2600 ሜ.ባ.ጠ.በ ሁሉም ወይና ደጋ አካባቢዎች | 11447 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለጥምር ደን እርሻ፣ ለአጥር፣ ለጥላ፣ ለህንጻ ግንባታ |
| *Acacia decurrens* | ሚሞዛ፣ አቃጫ | ከ1000-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ ሁሉም ወይና ደጋማና ደጋማ አካባቢዎች | 73465 | ኦርቶዶክስ | በፈላ ዉሃ ዘሩን ለ24 ሰአት መዘፍዘፍ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለአጥር፣ ለጥላ፣ ለአካባቢ ውበት፣ ለንፋስ መከላከያ |
| *Alibiza lebbeck* | የውጭ ሰሳ፣ አምባቤሳ | ከ500-1500 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅ እና ርጥብ ቆላማ አካባቢዎች | 9454 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለጥላ፣ ለዉብት፣ ለንብ ማነብ |
| *Acacia melanoxylon* | አሜድላ | ከ700-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ ሲሆን በሁሉም እርጥብ ቆላማ፣ ወይናደጋማና ደጋማ አካባቢዎች | 84592 | ኦርቶዶክስ | በፈላ ዉሃ ዘሩን ለ24 ሰአት መዘፍዘፍ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለከሰል፣ ለአካባቢ ውበት፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለጥላ፣ ለደን ጥምር እርሻ |
| *Acacia mollissima* | ሚሞዛ | ከ600-1700 ሜ.ባ.ጠ.በ በሁሉም በቆላ፣ እርጥብ ቆላማና በረሃ አካባቢዎች | 72910 | ኦርቶዶክስ | በፈላ ዉሃ ዘሩን ለ24 ሰአት መዘፍዘፍ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለከሰል፣ ለአካባቢ ውበት፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለጥላ፣ ለደን ጥምር እርሻ |
| *Acacia nilotica* | ጥቁር ግራር፣ ጨባ፣ ቦቁቂ | ከ600-1700 ሜ.ባ.ጠ.በ በሁሉም በቆላ፣ እርጥብ ቆላማና በረሃ አካባቢዎች | 7317 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለከሰል፣ ለማገዶ፣ ለቁሳቁስ መስሪያ፣ ለንብ ማነብ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለጥላ፣ ለጥርስ መፋቂያ፣ ለደን ጥምር እርሻ |
| *Acacia polyacantha* | ግማርዳ | ከ500-1600 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅና እርጥብ ቆላማ አካባቢዎች | 13722 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለሙጫ፣ ለእርሻ ቁሳቁስ መስሪያነት፣ ለአካባቢ ውበት፣ ለአጥር፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለንፋስ መከላከያ፣ ለመድሃኒትነት (ቅጠሉና ስሩ)፣ ለእንስሳት መኖ |
| *Acacia saligna* | አቃጫ | በደረቅና እርጥብ ቆላማ እንዲሁም ወይና ደጋ አካባቢዎች | 65734 | ኦርቶዶክስ | በፈላ ዉሃ ዘሩን ለ24 ሰአት መዘፍዘፍ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለአካባቢ ውበት፣ ለከሰል፣ ለአፈር ጥበቃ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *Acacia senegal* | ቆንጥር፣ ስባንሳ ግራር፣ ሲባንሳ ዲማ | ከ500-1700 ሜ.ባ.ጠ.በ ሁሉም በረሃማ በሆኑና ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 10615 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለሙጫ፣ ለቤት ውስጥና ለእርሻ ቁሳቁስ መሥሪያ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለአሳ መረብ መሥሪያ(ስሮቹ) |
| *Acacia seyal* | ቢጫ ግራር | ከ 500-2100 ሜ.ባ.ጠ.በ ሁሉም በረሃማ በሆኑና ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 17722 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለሙጫ |
| *Acacia tortilis* | ደወኒ ግራር፣ ጠዴቻ | ከ300-1900 ሜ.ባ.ጠ.በ በበረሃማ፣ ደረቅና እርጥብ ቆላማ አካባቢዎች | 14675 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለጥላ፣ ለአጥር፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለንብ ማነብ፣ ለእንስሳት መኖ፣ |
| *Azadirachta indica* | ኒም፣ ገለሎ | ከ400-1500 ሜ.ባ.ጠ.በ ሲሆን በደረቅና እርጥብ ቆላማ እንዲሁም እርጥብ ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 9631 | ሪካልሲትራንት | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለከሰል፣ ለንብ ማነብ፣ ለአካባቢ ውበት፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለመድሃኒትነት፣ ለጥላ፣ ለደን ጥምር እርሻ |
| *Balanites aegyptiaca* | በደኖ | ከ0-1800 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅና እርጥብ ቆላማ አካባቢዎች | 533 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ከ2-3 ዘር መዝራት | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለቁሳቁስ መስሪያ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለንፋስ መከላከያ፣ ለጥላ፣ ለአጥር፣ ለመድሃኒትነት |
| *Casuarina equisetifolia* | ሸውሸዌ፣ አርዘሊባኖስ | ከ0-2200 ሜ.ባ.ጠ.በ በቆላማና በወይና ደጋ አካባቢዎች | 1176470 | ኢንተርሚዴት | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለጣውላ፣ ለውበት፣ ለማገዶ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለጥላ፣ ለንፋስ መከላከያ፣ ለስልክ እንጨት፣ ለህንጻ ግንባታ |
| *Cajanus cajan* | የርግብ አተር | ከ1000-2400 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅና እርጥብ ቆላማ፣ ወይና ደጋማ እ ደጋማ አካባቢዎች | 7898 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በፖት ላይ ወይም በመድብ ላይ መዝራት | ለማገዶ፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለንፋስ መከላከያ፣ ለጥላ፣ ለቅርጫት መሥሪያ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለንብ ማነብ |
| *Callistemon citrinus* | ቦትል ብረሽ | ከ1200-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋማና በወይና ደጋማ አካባቢዎች | 4904365 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለውበት፣ ለመድሃኒትነት፣ ለአጥር |
| *Chamaecytisus palmenisis* | ትሪሉሰርን | ከ1700-3300 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 74200 | ኦርቶዶክስ | በፈላ ዉሃ ዘሩን መዘፍዘፍ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለደን ጥምር እርሻ ፣ ለአፈር ለምነት ለማገዶ፣ ለአጥር፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለንብ ማነብ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለንፋስ መከላከያ |
| *Cordia Africana* | ዋንዛ፣ ወዴሳ | ከ900-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋና በወይና ደጋ ቦታዎች | 6141 | ኦርቶዶክስ | በቀዝቃዛ ዉሃ ዘሩን ለ12 ሰዓት መዘፍዘፍ | በቀጥታ በፖት ላይ መዝራት | ለማገዶ፣ ለውበት፣ ለአፈር ጥበቃ፣ ለጥላ፣ ለንብ ማነብ፣ ለጥምር ደን እርሻ፣ ለጣውላ |
| *Cupressus lustanica* | የፈረንጅ ጥድ | ከ1500-3200 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢዎች | 156739 | ኦርቶዶክስ | በረጠበ አሸዋ ላይ ፍሪጅ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለአፈር ጥበቃ፣ ለጥላ፣ ለንፋስ መከላከያ፣ ለውበት፣ ለጣውላ፣ ለህንጻ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ውስጥ ለ 21 ቀናት ማስቀመጥ | | ግንባታ |
| *Cupressus pyremidals* | ሾጣጣ ጥድ | ከ1500-3200 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 146977 | ኦርቶዶክስ | በረጠበ አሸዋ ላይ ፍሪጅ ውስጥ ለ 21 ቀናት ማስቀመጥ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለውበት፣ ለጣውላ፣ ለመድሃኒትነት |
| *Delonix regia* | የድሬዳዋ ዛፍ | ከ200-1600 ሜ.ባ.ጠ.በ ሲሆን በደረቅና እርጥብ ቆላማ እንዲሁም እርጥብ ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 2961 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ በፖት ላይ መዝራት | ለጥላ፣ ለውበት |
| *Dovyalis caffra* | ኮሽም | ከ0-1800 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅና እርጥብ ቆላማ አካባቢዎች | 29446 | ሪካልሲትራንት | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ መዝራት | ለአጥርነት፣ ለምግብነት |
| *Dovyalis abyssinica* | ኮሽም | ከ1700-3000 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 33684 | ሪካልሲትራንት | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለአጥርነት፣ ለምግብነት፣ ለመድሃኒትነት |
| *Dodonaea angustifolia* | ክትክታ | ከ1000-2400 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅና እርጥብ ቆላማ፣ ወይና ደጋማ እና ደጋማ አካባቢዎች | 117259 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለጣውላ፣ ለንብ ማነብ፣ ለማገዶ፣ ለመድሃኒትነት |
| *Eucalyptus camaldulnesis* | ቀይ ባህር ዛፍ | ከ1200-2800 ሜ.ባ.ጠ.በ በደረቅና እርጥብ ቆላማ፣ ወይና ደጋማ እና ደጋማ አካባቢዎች | 1887507 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለምሰሶ፣ ለጣውላ |
| *Eucalyptus citriodora* | ሽቶ ባህር ዛፍ | ከ1800-2000 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ አካባቢዎች | 162882 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለምሰሶ፣ ለጣውላ |
| *Eucalyptus globulus* | ነጭ ባህር ዛፍ | ከ1700-2800 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 295857 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለምሰሶ፣ ለጣውላ፣ ለቪነር |
| *Eucalyptus grandis* | ቀይ ባህር ዛፍ | ከ1700-2800 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 3267974 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለምሰሶ፣ ለጣውላ፣ ለቪነር |
| *Eucalyptus saligna* | ቀይ ባህር ዛፍ | ከ1700-2300 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 2101282 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለምሰሶ፣ ለጣውላ፣ ለቪነር |
| *Eucalyptus viminalis* | ቀይ ባህር ዛፍ | ከ2000-3400 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 951656 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለምሰሶ፣ ለጣውላ፣ ለቪነር |
| *Ekebergia capensis* | ሶል | ከ1600-3000 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና | 1910 | ሪካልሲትራንት | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፤ ለጠዉላ፤ ለዉበት |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | | | | | |
| *Grevillea robusta* | ግራቪሊያ | ከ1500-2700 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 78751 | ኢንተርሚዴት | በቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ለ48 ሰዓት በማቆየት አውጥቶ መዝራት | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለውበት |
| *Hagenia abyssinica* | ኮሶ | ከ2300-3300 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 333577 | ኢንተርሚዴት | የዘሩን ሽፋን ማስወገድ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለውበት፣ ለመድሃኒትነት |
| *Jacaranda mimosifolia* | የውበት ዛፍ | ከ1200-2400 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋና በወይና ደጋ ቦታዎች | 98058 | ሪካልሲትራንት | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለውበት፣ ለማገዶ፣ ለጥላ |
| *Jatropha curcas* | አይደርቄ | ከ200-1600 ሜ.ባ.ጠ.በ ሲሆን በደረቅና እርጥብ ቆላማ እንዲሁም እርጥብ ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 2400 | ኢንተርሚዴት | በቀዝቃዛ ውሃ ለ2 ሰዓት መዘፍዘፍ | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለመድሃኒትነት፣ ለምግብነት፣ ለአፈር ለምነት፣ ለማገዶ |
| *Juniperus procera* | ያሀበሻ ጥድ | ከ1500-3300 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 55850 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለውበት |
| *Leucaena leucocephla* | ሉሲኒያ | ከ0-1600 ሜ.ባ.ጠ.በ በቆላማና በወይና ደጋ አካባቢዎች | 21437 | ኦርቶዶክስ | በፈላ ዉሃ ዘሩን ለ2 ደቂቃ መዘፍዘፍ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለጥምር እርሻ ደን፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለአፈር ጥበቃ |
| *Melia azedarach* | ሜሊያ | ከ0-2400 ሜ.ባ.ጠ.በ በቆላማና በወይና ደጋ አካባቢዎች | 4695 | ሪካልሲትራንት | ለ 3 ቀን በቀዝቃዛ ዉሃ ዉስጥ ማቆየት | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለውበት |
| *Millettia ferruginea* | ብርብራ | ከ1000-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋና በወይና ደጋ ቦታዎች | 11351 | ኢንተርሚዴት | አያስፈልገውም | በቀጥታ ፖት ላይ መዝራት | ለጥምር እርሻ ደን፣ ለአፈር ለምነት |
| *Moringa stenopetala* | ሺፈራው | ከ500-1700 ሜትር ከባ.ጠ.በ ሁሉም በረሃማ በሆኑና ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 1980 | ኦርቶዶክስ | የዘሩን ሽፋን ማስወገድ | በቀጥታ ፖት ላይ መዝራት | ለምግብነት፣ ለጥምር እርሻ ደን |
| *Olea africana* | ወይራ | ከ1400-3300 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 10020 | ኢንተርሚዴት | የዘሩን ሽፋን ማስወገድ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለከሰል |
| *Parkinsonia aculeata* | የኢየሩስ አሌም እሾህ | ከ300-1700 ሜ.ባ.ጠ.በ ሁሉም በረሃማ በሆኑና ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 11282 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለጥላ፣ ለውበት፣ ለንብ ማነብ |
| *Pinus patula* | ፓቹላ | ከ1900-3000 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 149700 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለውበት |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *Pinus radiata* | ራዲያታ | ከ2200-2300 ሜ.ባ.ጠ.በ በእርጥብና በጣም እርጥብ ወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች | 49693 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለውበት |
| *Podocarpus gracilior (Afrocarpus falcatus)* | ዝግባ | ከ1500-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋና በወይና ደጋ ቦታዎች | 1603 | ኦርቶዶክስ | የዘሩን ሽፋን ማስወገድ | በቀጥታ ፖት ላይ መዝራት | ለማገዶ፣ ለጣውላ፣ ለውበት |
| *Prunus africana* | ጥቁር እንጨት | ከ900-2600 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋና በወይና ደጋ ቦታዎች | 5289 | ኦርቶዶክስ | ጫፉን መቁረጥ | በቀጥታ ፖት ላይ መዝራት | ለጣውላነት፣ ለማገዶ |
| *Pterolobium stellatum* | ተሳቢ ቆንጥር | ከ1200-2500 ሜ.ባ.ጠ.በ በደጋማና በወይና ደጋማ አካባቢዎች | 34045 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለጥምር እረሻ ደን፣ ለአፈር ለምነት |
| *Schinus molle* | ቁንዶ በርበሬ | ከ0-2400 ሜ.ባ.ጠ.በ በቆላማና በወይና ደጋ አካባቢዎች | 28335 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በቀጥታ ፖት ላይ መዝራት | ለውበት፣ ለማገዶ |
| *Sesbania aculeata* | ሰስባኒያ | ከ300-2000 ሜ.ባ.ጠ.በ ሲሆን በደረቅና እርጥብ ቆላማ እንዲሁም እርጥብ ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 72643 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለመኖ፣ ለመድሃኒትነት፣ ለአፈር ለምነት፣ ለምግብነት |
| *Spathodea nilotica* | የጫካ ነበልባል | በደረቅና እርጥብ ቆላማ እንዲሁም ወይና ደጋ አካባቢዎች | 205939 | ሪካልሲትራንት | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለውበት፣ ለማገዶ፣ ለጥላ |
| *Tamarindus indica* | ሁመር፣ ሮቃ | ከ0-1500 ሜ.ባ.ጠ.በ በቆላማና በወይና ደጋ አካባቢዎች | 2174 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለጣውላ፣ ለምግብነት፣ ለመኖ፣ ለመድሃኒትነት |
| *Ziziphus macrocarpa* | ቁርቁራ | ከ400-1600 ሜ.ባ.ጠ.በ ሁሉም በረሃማ በሆኑና ወይና ደጋማ አካባቢዎች | 2542 | ኦርቶዶክስ | አያስፈልገውም | በቀጥታ በፖት ላይ ወይም በመደብ ላይ ተዘርቶ ወደ ፖት ማዛወር | ለምግብነት፣ ለመድሃኒትነት፣ ለጥምር እረሻ ደን |

## ምህፃረ ቃል

| | |
|---|---|
| **ኪ.ግ** | ኪሎግራም |
| **ሜ.ባ.ጠ.በ** | ሜትር ከባህር ጠለል በላይ |

## መፍቻ

| | |
|---|---|
| **ኦርቶደክስ** | ዝቅተኛ የርጥበት መጠን የሚፈልግ እና የተሻለ የቆይታ ጊዜ ያለዉ |
| **ሪካልሲትራንት** | ከፍተኛ የርጥበት መጠን የሚፈልግ እና አጭር የቆይታ ግዜ ያለዉ |
| **ኢንተርሚዴት** | መካከለኛ የርጥበት መጠን የሚፈልግ ሲሆን የዘሩ የቆይታ ጊዜ በጨመረ ቁጥር የብቅለት አቅሙ ይቀንሳል |
| **የዘር ቅድመ መዝራት ህክምና** | ዘሩን ከመዝራት በፊት መደረግ የለበት የብቅለት ማሻሻያ ዘዴ |